# ቅድስት ድንግል ማርያም ከልደት እስከ ዕርገት



የዛሬ 2ሺህ ዓመት ገደማ በምድረ ይሁዳ የሚኖሩ ባልና ፣ ሚስት ነበሩ ፤ የወንዱ ስም ኢያቄም ፤ የሚስቱ ስም ደግሞ ሐና ይባላል። ኢያቄም ትውልዱ ከዳዊት ቤት (ወገን) ሲሆን ፣ ሐና ከቤተ አሮን ትወለዳለች። ባልና ሚስቱ እግዚአብሔርን የሚወዱ ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ደጋግ ፍጥረቶች ነበሩ። ልጅ ባለ መውለዳቸውም ብዙ ዘመን ጠብቀውና እግዚአብሔርን ደጅ ጠንተው እጅግ ሲያዝኑ ይኖሩ ነበር። በስተርጅና ዘመናቸውም እንኳ ተስፋ ባለመቁረጥ ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ፈጣሪያቸውን አጥብቀው ለመኑት ፤ የሚወለደውም ልጅ ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ ይኾን ዘንድ ብፅአት ገቡ (ተሳሉ)። የእምነታቸውም ፅናት እንግዲህ እስከዚህ ነበር።

እንደ ቤተ ክርሰቲያናችን ትውፊትም ፣ ሐና እና ኢያቄም ሐምሌ 30 ቀን ሕልም አዩ። እግዚአብሔር በገለጸላቸው ራዕይ መሠረት ነሐሴ 7 ቀን ድንግል ማርያም ተፀነሰች። ሃናም በፅንሷ ወራት በሽተኞች ልብሷን እየነኩ ከደዌያቸው ስለተፈወሱ፤ ዐይነ ስውራንም ዓይኖቻቸው ስለበሩላቸው፤ ምቀኞች ተነስተው ሐናን ሊጣሏት፤ አልፈውም በድንጋይ ሊወግሩዋት ፈለጉ።

በዚያን ጊዜ ፣ የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄም ተገልጸ <<ወደ ሊባኖስ ተራራ ይዘሃት ውጣ» አለው ። ይዟትም ወጣ። በዚያም እንዳሉ ግንቦት 1 ቀን ድንግል ማርያም በአንድ ዋሻ ውስጥ ተወለደች። ሃናና ኢያቄምም ስለታቸው ስለሰመረ ፣ በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት ፣ ድንግል ማርያምን 3 ዓመት ሲሞላት ሕፃንዋን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው በዚያ እንድታድግ ሰጡ። ድንግል ማርያምም በቤተ መቅደስ 12 ዓመት ኖረች።

እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት ቀን በየዓመቱ ታህሳስ 3 ቀን በደመቀ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያናችን ይከበራል። እመቤታችን በቤተ መቅደስ በነበረችበትም ጊዜ እንደ ሌሎቹ ደናግለ እሥራኤል ኹሉ ሃርና ወርቅ እያስማማች በመፍተል፤ ውሃ በመቅዳት ታገለግል ነበር። እንደ ሥርዓቱም ዕድሜዋ ለአቅመ ሄዋን በደረሰ ጊዜ ፣ በቤተ መቅደስ መኖር ስለማይፈቀድ ፣ ለዐረጋዊው ዮሴፍ በዕጮኝነት እንዲጠብቃት ተሰጠው።

በትንቢቱ መሠረት የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰም ጊዜም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ድንግል ማርያም ተላከ።

መልአኩም ወደ እርስዋ ገባ። ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ፥ ደስ ይበልሽ ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ የተነሣ በጣም ደነገጠች። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆ ፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ፤ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ፤ በያዕቆብም ቤት ለዘለላም

ይነግሣል ፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም። ማርያምም በመገረም መልአኩን። እኔ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለችው።

መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ ፥ በስተርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች ፥ መካን ትባል ለነበረችው ለእርስዋ ይህ ስድስተኛ ወርዋ ነው ፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። ጌታም ቃልዋን ምክንያት አድርጎ ያኔውኑ በማሕፀንዋ አደረ። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።

ይህ በእንዲህ እያለ እጮኛዋ ዮሴፍ ድንግል ማርያም መጽነስዋን እንዳወቀ ፤ ጻድቅ ሰው ነበረና ሊገልጣት አልወደደም ፤ ስለዚህም በስውር ሊተዋት አሰበ። በዚህ ጊዜም እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው ፥ እንዲህም አለው ፤

የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ። እነሆ ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው ፤ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል ፤ ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ ፤ እጮኛውንም ወሰደ።

የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን በደረስ ጊዜ የሮማ ንጉሠ ነገሥት አውግስጦስ ቄሣር በግዛቱ የሚገኙ ዜጎች ሁሉ እንዲመዘገቡ ቁጥራቸው እንዲታወቅ ትእዛዝ አወጣ። እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ። ዮሴፍም ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ አውራጃ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ 35 ኪሎሜትር ላይ ርቃ ወደምትገኘው ወደ ዳዊት ከተማ ቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ።

በዚያም በቤተልሔም ሳሉ ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ወራት ደረሰ። በከተማውም የእንግዶች ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው ቅድሰት ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ያደሩት በከብቶች በረት ነበር። በዚያችም ሌሊት ሰማይና ምድርን የፈጠረው፤ ሁሉ የእርሱ የሆነው የዓለም መድኃኒት አማኑኤል ራሱን ዝቅ ዝቅ አድርጎ በከብቶች በረት ተወለደ። ድንግል ማርያምም በመጠቅለያ ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው። ወራቱም ብርድ ስለነበር ከብቶች በትንፋሻቸው አሞቁት።

ለመገረዝም ስምንት ቀን በሞላው ጊዜ ፥ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ ፥ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ። እንደ ሙሴም ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ ፥ እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ሕግ በጌታ ፊት ሊያቆሙትና መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ይዘውት ወጡ።

እነሆም ፥ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ ፥ ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር ፤ ጻድቅና ትጉም ነበረ ፥ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ። በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። በመንፈስም ወደ መቅደስ ወጣ ፤ ወላጆቹም እንደ ሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን በአስገቡት ጊዜ ፥ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው እግዚአብሔርንም እየባረከ እንዲህ አለ።

ጌታ ሆይ ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ፤ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው። ዮሴፍና እናቱም ስለ እርሱ በተባለው ነገር ይደነቁ ነበር።

ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምንም ፤ እነሆ ፥ የብዙዎችን ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ ፥ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል ፥ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት።

ከአሴር ወገን የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች ፤ እርስዋም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች ፤ እርስዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም ዐርጅታ ነበር ፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር። በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች ፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር።

በዚያን ዘመን የይሁዳ ገዥ የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ በኮከብ እየተመሩ ከምስራቅ ከመጡት ከሰብአ ሰገል ስለ ጌታ መወለድ ሰምቶ ስለነበር ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄመርምረው ሲመለሱ ፣ ለእሱም እንዲነግሩትና እሱም ደግሞ በተራው ሄዶ እንዲሰግድለት ንገሩኝ ብሏቸው ነበር። ይሁን እንጂ ሰብአ ሰገል ለተወለደው ንጉሥ መባቸውን ካቀረቡ በኋላ ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሕልም ስለተረዱ በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ተመለሱ።

እነርሱም ከሄዱ በኋላ ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታየው። እነሆ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ፤ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን እንዲሁም ሰሎሜን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ።

ሄሮድስም ሰብአ ሰገል እንደ ተሣለቁበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቈጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ አስገደለ።

በስደታቸው ምድር በታችኛው (ከታሕታይ) ግብጽ ዐልፈው እስከ ላይኛው (ላዕላይ) ግብፅ ለሦስት ዓመት ተኩል ቆይተዋል። ይህም በነቢዩ በሆሴዕ ልጄን ከግብፅ ጠራኹት የተባለው እንዲፈጸም ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ ፥ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታየው ፤

<u>የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ።</u>

እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ እስራኤል አገር ገባ። በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ፥ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ። ሕፃኑ ኢየሱስም ዐደገ ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ። ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር። እሱም ይታዘዝላቸው ነበር።

ክርስቶስም 30 ዓመት በሞላው ጊዜ በዮርዳኖስ ባሕር በመጥምቁ ዮሐንስ ተጠመቀ ፤ ያኔውኑም ወደ ቆሮንቶስ ተራራ ሄደ ፤ 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾመ፤ ወደ ገሊላ ተመልሶም መጣ። ወዲያውም የእግ ዚአብሔርን መንግሥት መስበክ ጀመረ። በቃና ዘገሊላም ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሰርግ ላይ ተገኘ። በዚሁ ሰርግ ላይ የድግሱ ወይን አልቆ ሲጨነቁ፤ ድንግል ማርያም ለልጅዋ የወይን ጠጅ እኮ አ ለቆባቸዋል ባለችው ጊዜ፤ በእርሷ አሳሳቢነት ሳያመነታ ጌታ ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ለወጠው።ከጣ እሙም የተነሣ ብዙዎች ተደነቁ። ይኽም ወንጌለ መንግሥትን መስበክ ሲጀምር ጌታ ያደረገው የመጀመ ሪያው ተአምር ሆነ።

ክርስቶስም በመዋዕለ ሥጋዌው ፣ በዚች ምድር ላይ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ወንጌለ መንግሥትን ካስተማ ረ በኋላ በአይሁድ እጅ ፀዋትወ መከራን እየተንገላታ ሲቀበል፤ ድንግል ማርያም ልጅዋን አልተለየችው ም ነበር። በቀራንዮም በእግረ መስቀሉ ሥር ከወንጌላዊው ከዮሐንስና ከሌሎችም ሴቶች ጋር እያለቀሰ ች ቆማ ፣ ዐረጋዊ ስምዖን እንደተናገረው ፣ ልብዋ በሐዘን ሰይፍ ቆስሎ ፣ ዕንባዋን በደረትዋ እንደ ስን ውሀ ታፈሰው ነበር። ኢየሱስም እናቱንና ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር ዮሐንስን በአጠገቧ ቆሞ ባየው ጊዜ እናቱን ፤ አንቺ ሴት ፥ እነሆ ልጅሽ አላት፤ ደቀ መዝሙሩንም እነኋት እናትህ አለው። ከዚያችም ሰዓት አንስቶ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

ክርስቶስ ከመቃብር ተነሥቶ ካረገም በኋላ ፣ እመቤታችን ከወንጌላዊው ከዮሐንስ ጋር በደብረ ጽዮን ስ ትኖር ቆይታ በ64 ዓመቷ ከዚህ ዓለም ጣር በሞት ተለየች። ሐዋርያትም አስከሬኗን በጌቴ ሰማኒ አሳረፉ።

ከሶስት ቀንም በኋላ ከሙታን ተለይታ ተነስታ ወደ ሰማይ ወደ ልጅዋ፤ ወደ ፈጣሪዋ አረገች። የዚች የ ተባረከች ፣ የተቀደሰች እናታችን የእመቤታችን ዋናው ሥራዋ በቤተ መቅደስ እንደነበረችበት ጊዜ ፣ ሐርና ወርቅን አስማምቶ መፍተል ሳይሆን ፣ ስለ ኃጥአን ነፍስ ያለ ዕረፍት መለመን መማለድ ነው። ልመናዋና ክብሯ ለዘላለም በእኛ ላይ ይኑር።

በእደ ማርያም እጅጉ (ጥቅምት 2006)